የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፯
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.77
ADDIS ABABA 26th Augest, 2020


## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፸፫/፳፻፲፪ ዓ.ም


የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..........ገጽ ፲፪ሺ፯፻፶፭


## Content

Regulation No.473/2020


the Institute of Strategic Affairs Establishment Council of Ministers Regulation..............Page 12,755


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፫/፳፻፲፪

## የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፳፻፲፩ አንቀጽ ፭ እና ፴፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፫/፳፻፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፤በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ሚኒስቴር" ወይም “ሚኒስትር” ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪/ "ኢንስቲትዩት" ማለት የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.473/2020

## COUNCIL OF MINSTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE INSTITUTE OF STRATEGIC AFFAIRS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.1097/2018.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "the Institute of Strategic Affairs Establishment Council of Ministers Regulation No.473/2020."

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1/ “Ministry or Minister” means the Ministry or Minister of Foreign Affairs;

2/ “Institute” means the Institute of Strategic Affairs;

፫/ “ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች” ማለት ሀገራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለምአቀፋዊ የሰላም፣ የፀጥታና ደህንነት፣ የውቅረ-መንግሥት፣ የሀገረ መንግሥት፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ህገ መንግስታዊነት፣ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀሳባዊ፣ ህጋዊና ተቋማዊ የፖሊሲና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ያካትታል፤

3/ ‘‘Strategic Affairs’’ means national, regional and global peace, security & stability, state building, nation building, democratization, constitutionalism, social, historical, conceptual, legal, and institutional policy and strategic affairs;

፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል፡፡

4/ any expression in a masculine gender includes the feminine.

## ፫. <u>መቋቋም</u>

## 3. <u>Establishment</u>

፩/ የስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ “ኢንስቲትዩቱ” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

1/ The Institute of Strategic Affairs (hereinafter referred to as “the Institute") is here by established as an autonomous Federal government institution having its own legal personality.

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

## ፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## 4. <u>Headquarters</u>

The Institute shall have its headquarters in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## ፭. <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማ</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

## 5. <u>Objectives of the Institute</u>

The Institute shall have the following objectives:

፩/ የሀገሪቱን የሰላም የደህንነትና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት በማድረግ የምርምር ስራዎችን፣ ጥናቶችን፣ ትንተናዎችን፣ ሴሚናሮችን፣ አውደጥናቶችን፣ የውይይትና የገለፃ መድረኮችን በማከናወን አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ምክረ ሀሳብ የማቅረብ፤

1/ Develop alternative policy options and recommendations through carrying out actionable policy research, studies and analysis; organize seminars, workshops, discussions and lectures based on the country’s peace, security and foreign policy and strategy;

፪/ የሀገር ውስጥ፣ አካባቢያዊ፣ ቀጠናዊና ዓለምአቀፋዊ የሰላም፣ የፀጥታና የደህንነት ኩነቶች፣ ክስተቶች፣ ስጋቶችና አዝማሚያዎች ላይ የምርምርና የጥናት ተግባራትን በማከናወን የልህቀት ማዕከል ሆኖ የማገልገል፤

2/ serve as a center of excellence in research and undertake studies on peace and security, events, threats and trends at national, regional and global levels;

፫/ የውቅረ-መንግስት፣የሀገረ-መንግስት፣የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና ሕገ መንግስታዊነት, ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀሳባዊ፤ ህጋዊና ተቋማዊ መሰረት ጥናቶችን ፣ትንተናዎችን፣ሴሚናሮችን ፣ዐውደ ጥናቶችን፣ የውይይት እና የገለፃ መድረኮችን በማከናወን አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ምክረ ሃሳብ የማቅረብ፤

፬/ ሰላምና መረጋጋት ይበልጥ እንዲጐለብት የሚረዱ የግንዛቤና የክህሎት ማስፋፊያ ስልጠናዎችን የማካሄድ፡፡

## ፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ዓበይት የሆኑ ሀገራዊ፣ ክፍለ ዓለማዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የመተንተንና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፤

፪/ ሀገራዊ የሰላም፣ ደህንነትና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም አፈፃፀም ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ አማራጭ የአፈፃፀም ሥልቶች ላይ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፣ፀ፤

፫/ በሰላምና ደህንነት ፣ ሀገራዊ መግባባት፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የውጭ ግንኙነት ዙሪያ በጥናትና መረጃ የተደገፈ የማማከር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፬/ የሰላምና ደህንነት፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የውጭ ግንኙነት በሚመለከቱ ጉዳዮች አጫጭር ሥልጠናዎችን እንዲሁም ሴሚናሮች፣ ዐውደ ጥናቶች፣ ሲምፖዚየሞች፣ ጉባዔዎች እና ሌሎች የዕውቀት፣ የልምድ ልውውጥና የክርክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፭/ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር ግንኙነት ይመሰርታል፣ የጋራ መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፮/ የጥናት እና የምርምር ውጤቶችን ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤

3/ develop alternative policy options and recommendations through carrying out actionable policy research, studies and analysis on the social, historical, conceptual, legal and institutional foundations of state building, nation building, democratization and constitutionalism; organize seminars, workshops, discussions and lectures in the areas of peace, and security;

4/ conduct awareness raising and skill development trainings that help consolidate peace and stability.

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the following powers and duties:

1/ collect and analyze information and undertake research on major national, regional and global issues;

2/ conduct studies and research on national peace and security, and foreign policy and strategy and on the implementation of these policies with a view to identify and propose alternative strategies of implementation;

3/ provide research and evidence based consultancy on issues of peace and security, national consensus, democratization, foreign policy and other strategic issues;

4/ organize short term trainings, seminars, workshops, symposia, conferences and other knowledge and skills exchange and debate platforms on peace and security, democratization and foreign policy;

5/ establish partnerships, networks and cooperation and organize joint forums with international organizations, governmental and non-governmental institutions with similar objectives;

6/ publish and disseminate research and study findings;

፯/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፰/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. አደረጃጀት

ኢንስቲትዩቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፪/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

## ፰. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፤ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞችና ተመራማሪ ዎች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ መርሀ ግብሮች አዘጋጅቶ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

መ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለመንግሥት ቀርቦ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት የሥራ መርሀ ግብርና በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ሰ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች ያዘጋጃል፡፡

7/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

8/ Undertake other activities necessary to realize its objectives.

## 7. Organization of the Institute

The Institute shall have:

1/ An Executive Director and, as may be necessary, Deputy Executive Directors, to be appointed by the Government; and

2/ The necessary staff.

## 8. Powers and Duties of the Executive Director

1/ The Executive Director shall be the chief executive officer of the Institute and shall, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Executive Director shall in particular:

a) exercise the powers and duties of the Institute provided under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Institute in accordance to the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Council the program of work of the Institute and implement the same as per the Council's recommendation;

d) prepare annual budget of the Institute and submit to the Council for advice and implement it upon approval by the government;

e) effect expenditure in accordance with the approved annual plan and budget of the Institute;

f) represent the Institute in its dealings with third parties;

g) prepare and submit to the Council the operational and financial reports of the Institute.

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣን እና ተግባራቱ በከፊል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፱. የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

ሀ) የኢንስቲትዩቱን ሥልጣን እና ተግባራት አፈፃፀም በሚመለከት ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

ለ) በተመደቡበት የሥራ መስኮች የሚከናወኑ ተግባራትንና ፕሮጀክቶችን ሥራ ይቆጣጠራሉ፤

ሐ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ መመሪያዎችን እና ውሳኔዎችን አፈፃፀም ይከታተላሉ፣ ያስፈጽማሉ፤

መ) በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር የኢንስቲትዩቱን ሥራ ይመራል፣ያስተባብራል፡፡

## ፲. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል፡፡

## ፲፩. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

፫/ ኢንስቲትዩቱ የውስጥ ኦዲተር ይኖረዋል፡፡

## ፲፪. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

፩/ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፯/፪ሺ፯ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

3/ The Executive Director may delegate part of his powers and duties to the extent necessary for efficient performance of the activities of the Institute.

## 9. Powers and Duties of the Deputy Executive Directors

1/ The Deputy Executive Directors shall:

a) assist the Executive Director in the implementation of the Institute's powers and duties;

b) supervise activities and projects assigned to their respective positions;

c) follow up the implementation of the directives and decisions of the Executive Director with respect to their respective positions;

d) Perform other activities assigned to them by the Executive Director.

2/ In the absence of the Executive Director, the delegated Deputy Executive Director shall lead and coordinate the activities of the Institute.

## 10. Budget

Budget of the Institute shall be allocated by the government.

## 11. Books of Accounts

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and other financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by an Auditor designated by the Auditor General.

3/ The institute shall have an internal Auditor.

## 12. Repeal and Inapplicable Laws

1/ The Ethiopian Foreign Relations Strategic Studies Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 347/2015 is hereby repealed.

፪/ ይህን ደንብ የሚቃረኑ ሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## ፲፫. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፯/፪ሺ፯ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂያዊ ጥናት ኢንስቲትዩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

## ፲፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**አብይ አሕመድ(ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ No Regulation and Directive may, in so far as it is inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to matters covered under this Regulation.

## 13. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Ethiopian Foreign Relations Strategic Studies Institute Established under Regulation No. 347/2015 are hereby transferred to the Institute.

## 14. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa, on this 26th day of Augest, 2020.**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**